# በአምሃራው ላይ የተፈጸመ የዘር ፍጅትና (Amhara Genocide) የጎልውና ትግሉ

From MG

ፍጡር ሊሸከመው ከሚችለው በላይ የተፈጸመ ታላቅ ፍዳን፣ መከራን፣ ግድያንና ጭፍጨፋን ስናጠና በናዚ ጀርመን ወቅት የነበሩ እስራኤሎች ላይ የተደረገው የዘር ፍጅት (Holocaust)፣ የቦስንያ ጭፍጨፋ(Bosnia Genocide)፣ እንዲሁም የአርመኖች ጭፍጨፋ (Armenian Genocide) ከፊታችን ድቅን ይላል። በአፍሪካም የሩዋንዳው እልቂት (Rwandan Genocide) ከነዚሁ ጋር አብሮ የሚደመር ዘግናኝ ታሪክ ነው። ናዚ እስራኤሎችን ለማጥፋት አስቀድሞ ከፍተኛ መረጃን ሲሰበስብ ቆይቷል። ምንም እንኳን ከሌላው የህብረተሰብ ክፍል ጋር ልቅ ቅርርብ የማያደርጉ ቢሆንም - እስራኤሎች ምን እንደሚበሉ፣ ምን እያሉ እንደሚጸልዩ፣ ኃይማኖታዊ ምሥጢሮቻቸውና ከቤተሰቦቻቸው ጋር እንኳን ምን ዓይነት ግኑኝነት እንደሚያደርጉ እነሱን መስለው በተጠጓቸው ጓደኞች፣ የሥራ ባልደረቦችና ረዳት መስለው በቀረቧቸው ግለሰቦችይመረጅ ነበር። እስራኤሎች ትውፊቶቻቸው፣ ምሳሌአዊ አነጋገሮቻቸው፣ ባጠቃላይ ሁለንተንዊ እንቅስቃሴዎቻቸውና ፈሊጦቻቸው ሳይቀር በናዚዎች እየተመዘገበ ምርመራና ጥናት ይደረግበት ነበር። እነሆ ታድያ ናዚዎች "ይግደራደሩናል፣ ዓላማችንን ያሰናክላሉ፣ በጸሎት ኃይል እርምጃዎቻችንን ይገታሉ" የሚሏቸውን እስራኤሎች አስቀድመው ካላጠፉ በቀር እርካታና ሠላም ማግኘት አልቻሉም። እስራኤሎች በእነሱ ላይ ከተፈጸመው ተሞክሮ ተነስተው ነው ዛሬ በመረጃና ጸረ-መረጃ ሙያ የላቀ ሥፍራን የተጎናጸፉት። ከላይ የጠቀስኳቸው ዓይነት የዘር ማጥፋት ሠለባ በመሆን ላይ ከሚገኙት መካከል አንዱ ነገድ በኢትዮጵያ ምድር የሚገኘው አማራ ነው።

አማራ በሰሜንና ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ደጋው ላይ የሠፈረ ነገድ ነው። እንደ ፈረንጆቹ አቆጣጠር በ2007 በተደረገው የሕዝብ ቆጠራ መሠረት የአማራ ሕዝብ ወደ 29 867 817 ይጠጋል ይላል ዊኪፔድያ ላይ የተጻፈ ማስረጃ። ከጠቅላላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ማህል32,5% ይሆናል ማለት ነው። የአማራው ነገድ ቋንቋ የሆነው አማርኛ በጎንደር፣ ጎጃም፣ ወሎ (ቤተ አምሃራ) እንዲሆም ሰሜን ሸዋ ውስጥ ይነገራል። የአማርኛ ቋንቋ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቋንቋ እንዲሁም በየዘመናቱ ለሚነሱት ገዥዎች የመንግሥት የሥራ ቋንቋ ነው። ባለ ለም መሬቱ አማራ ደሃ ነው። መሥራት አቅቶት አይደለም - በየዘመናቱ የሚነሱት የኢትዮጵያ ጠላቶችን ስለሚዋጋ እንጂ። አማራዎች ናቸው ተብለው የተፈረጁት ያለፉት ዘመን ገዥዎች ለክልሉ አንዳች አላደረጉለትም። አማራ ደሃም ቢሆን ድህነቱ ግን እምነቱንና ጀግንነቱን አይፈታተንበትም። አማራው እግዚአብሄርን በጽኑ ያምናል። አማራው እግዚአብሄርን ቀርቶ ካህናቱን ቀሳውስቱንና ገዥዎቹን ሳይቀር ያከብራል። "እንዳልኮራ ደሃ ነኝ፤ እንዳልፈራ ጎንደሬ ነኝ" ተብሎ የተጻፈው አንድ መፈክር የአማራውን ምንነት አጉልቶ ያሳያል። አማራ ትዕግስተኛ ነው። አማራ አማኝ ነው። አማራ የልቡን አይደብቅም። አምሃራ ቆራጥም ነው። አማራ - አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ባንዲራውንና ሃገሩ ኢትዮጵያን እንደ ዓይኑ ብሌን ይጠብቃል። ታድያ ምን በደል ኖሮበት ነው አምሃራው እንዲያልቅ የተፈረደበት?

ከመቸውም ጊዜ በላይ ዛሬ በየአማሮች ቤት ዘራቸው እንዲጠፋ በተፈለገበት ምክንያት ላይ የሃሳብ ልውውጥ ይደረጋል። አንዳንዶች "አማራ ጥንት በብሉይ ዘመን ከእስራኤሎች ጋር በነበረው ግኑኝነት ምክንያትይሆን በአረቦቹ የተጠላው? ሲሉ ይጠይቃሉ። ሌሎች ደግሞ "በቅኝ ግዛቱ ወረራ ወቅት ቆራጥ ተጋድሎ ያደረጉት አማሮች ብቻ ናቸው ተብሎ ተወርቶብን ይሆን ፈረንጆቹ የጠሉን" ሲሉ ሌላ ጥያቄ ይሠነዝራሉ።"እኛ አማራ ነኝ ከማለት ይልቅ - ኢትዮጵያዊ ነን - በማለታቸው ነው ጥርስ የተነከሰብን" እያሉ በሃዘን የሚናገሩም አይጥፉም። በዛ ያሉ አማሮች "ገዥዎች የአማርኛ ቋንቋ ስለሚናገሩ የፖለቲካው ጭቆና የተደረገውበመላው አማራው ትብብር ነው በሚል የተሳሳተ አስተሳሰብ ሊሆን ይችላል እንድናልቅ የተፈረደብን" ሲሉ ምርር ብለው ያለቅሳሉ። ሁሉም የመሰለውን እንደምክንያት ያቀርባል፤ ትክክለኛውን ለማወቅ ግን በዚህ ጉዳይ ላይ የፖለቲካ፣ ህግ ወይም የታሪክ ተመራማሪዎች ወደፊት ጥናት ያደርጉበት ይሆናል። ወያኔና ሻዕቢያ አማራው ነገድ ለምን እንዲጠፋ ፈለጉ - የሚለውን ስንቃኝ - በሃያ አምስት ዓመታት ውስጥ በአማራ ላይ የተፈጸመው ዘግናኝ የዘር ማጥፋት በደሎች ድቅን ይሉብናል። አቶ ስብሃት "አማራና ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስትያን አከርካሬቸው ተሰብሯል፣ ከዚህ በኋላ አያንሰራሩም" ሲል በትዕቢት የተናገረው አረፍተ ነገር ወያኔ አማራውን ለማጥፋት ያቀነባበረው ምስጢራዊ ተልዕኮ በከፊልም ቢሆን መስመር መያዙን ይጠቁማል። ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ አማራውን ከእልቂት ለማዳን ገና በጠዋቱ ያቋቋሙት "መላ አማራ ሕዝቦች ድርጅት" (መአሕድ) በወቅቱ ብዙዎች አማሮች ኢትዮጵያዊነትን ያዳክማል ሲሉ ሳይቀበሉት ቀርተው ነበር። ዛሬ ከብዙ ጥፋት በኋላ ግን ከአቶ ስብሃት አፍ ያፈተለከው አነጋገር በርካታ አማሮችን ከአሸለቡበት አንቅቷል። ያለፈው አልፏል ከአሁን ወድያ ግን አማራው በቅጡ ተደራጅቶ ወደ ፕሮፌሰር አስራት ምክር በመመለስ በወያኔ የሚተገብረውን አማራውን የማጥፋት ዕቅድ በህብረት ማምከንይኖርብናል።

**የአማራው መደራጀት ለምን አስፈለገ?**

አማራው ነገድ ጨርሶ እንዲጠፋ አልያም አንገቱን ደፍቶ ተሸማቆ እንዲቀር በትግሬዎች ነፃነት ስም የሚነግዱት ኤርትራውያን - ናዚዎች በእስራኤሎች ጋር ካደረጉት ያልነሰ ግፎችን በመፈጸም ላይ ይገኛሉ። ወያኔምናልባት የቀረው ነገር ቢኖር ነገዱን ሁሉ በማጎርያ ካምፖች አጉሮ ማመንመንና በመርዝ ጭስ መጨረስ ነው። በእርግጥ ይህም አልተደረገም አይባልም። ዛሬ የአማራው ወጣቶች በብር ሸለቆና በምስጢራዊ እስር ቤቶች ታስሮ ፍዳውን እያየ ነው። የአማራው ቁጥር በሃያ ዓመታት ውስጥ በሁለት ተኩል ሚሊዮን ማሽቆልቆሉ በራሱ በወያኔው ፓርላማ ውስጥ አንድ ወቅት ተነስቶ ነበር። በዚህ ጉዳይ ላይ በድፍረት የሚናገሩተቆርቋሪዎችን ድምጽ ለማፈን የፓርላማው አፈጉባዔ የነበረው አሻንጉሊቱ ተሾመ ቶጋ ጉዳዩን አድበስብሶ ስብሰባው እንዲቋረጣ በማድረግ የሎሌነቱን ድርሻ ተወጥቷል። ሌላው አሻንጉሊት ሽፈራው ሽጉጤም አማራው ከደቡብ ክልል እንዲፈናቀል ቀላል ያልሆነ የታማኝ ሎሌነት ግፍ በአማራው ነገድ ላይ ፈጽሟል። ይህ ሁሉ ግፍ በበደኖና በአርባጉጉ ከተፈጸሙት ዘግኛን ግድያዎች በኋላ የተከናወነ ነው። ድህነትን(poverty) ባክቴርያ፣ ነቀርሳንና ኤድስን (bicteria, tuberclosis, AIDS) ሆን ብሎ በአማራው ክልል ማስፋፋት፣ የወሊድ መቆጣጠርያ እንክብል በመስጠትና ማምከኛ መርፌ በመውጋት (birth control – contraception) ተፈጥሯዊ መራባትን ማጨናገፍ እንዲሁም በመርዛማ ማዳበርያ ምርታማነትን መቀነስና ለጤንነት ተስማሚ ያልሆነ ገዳይ ሰብል እንዲበቅል ማድረግ (genetically modified crops) በአማራ ላይ የተፈጸሙ ጥቂቶቹ የግፍ ሥራዎች ናቸው። ዘርን ማጥፋት ማለት ግድያ፣ በሰውነት ወይም ዓእምሮ ላይ የህመም ስሜት በመፍጠር ስነልቦናን መስለብ፣ ዘሩ በከፊልም ሆነ በሙሉ እንዲጠፋ ልዩ ልዩ ሰቆቃዎችን መፈጸም፣ መራባትን መግታትና ልጆችን እየሰረቁ በሌላ ቦታ ማዛወር ወይንም በበሽታ አስጠቅቶ እንዲሞቱ ማድረግ ነው። አማራው ላይ እነዚህ ግፎች ለመፈጸማቸው በራሱ በወያኔው ፓርላማ ለውይይት የተነሳው የበርካታ ከአምስት ዓመት በታች የአማራ ሕጻናት መሞታቸው ወይንም መጥፋታቸው ጉዳይ ራሱ ማስረጃ ነው። ይህን የጥፋት ተልዕኮ የሚያበረታቱ የውጭ ኃይላት ሊኖሩ እንደሚችሉ ፍንጮች ያሳያሉ። ወያኔ መርዛማ ማዳበርያዎችንና የወሊድ መከለከያ መድሃኒቶችን እንደምን አስገብቶ በአማራው ክልል ላይ ብቻ አርከፈከፈው የሚለውን ስናይ ለዚህ እኩይ ተግባር ትብብር የሚያደርጉ ጸረ አማራ ድርጅቶች ይኖራሉ የሚለው መላ ምት ግምት ውስጥ ይገባል። እነዚህ የውጭ ኃይሎች ምክንያታቸው ምናልባት ኢትዮጵያን የሚያህል መልካም የዓየር ጠባይና የተፈጥሮ ኃብት ያላትን ሃገር በቅኝ መግዛት አልያም መሬቷን መቀራመት ያልቻልነው በአማራው ተከላካይነት ምክንያት ነው የሚል የተሳሳተ ሃሳብ ሊሆን ይችላል። በእርግጥ በአጼ ቴዎድሮስ ተጀምሮ በአጼ ሚኒልክ አመራር ኢትዮጵያ በቅኝ ገዥዎች ላይ የተጎናጸፈችው ታላቅ ድል የቅኝ ገዥዎችን ህልም ከፉኛ ያጨለመ ነበር። በአድዋ ውጊያ ግን ያልተሰለፈ ኢትዮጵያዊ አልነበረም። ኦሮሞው፣ አማራው፣ ትግሬው፣ ወላይታው፣ ሲዳማው፣ ከንባታው፣ አፋሩ፣ ኮንሶውና ሌሎችም በውጊያው ላይ ነበሩ። አረቦቹም አማራውን አይወዱም ይባላል። ለምን ለሚለው ጥያቄ አንዳንዶች ኃይማኖታዊ ትንተና ሲያቀርቡ አንዳንዶች ደግሞ የአባይ ወንዝ ምንጭ የአማራው ሃገር መሆኑ በአረቦቹ ልቦና ውስጥ ቅናት አሳድሮ ሊሆን ይችላል ይላሉ።

የአማራው ነገድ መደራጀትና መሰባሰብ ዛሬ ከምንም በላይ አንገብጋቢ ሥራ ነው። ወያኔ ሥልጣኑን ከያዘ እስከ ዛሬ ሃያ አምስት ዓመት ድረስ ከአምስት ሚሊዮን በላይ የአማራ ሕዝብ ቁጥር ቀንሷል። እነሆ ታድያ የአማራው መደራጀት የፖለቲካ ሳይሆን የኅልውና ጉዳይ ነው። ይህ ጉዳይ ነገ ዛሬ የማይባል አፋጣኝ፣ ነገድን ከዕልቂት የመጠበቅ ታላቅ ኃላፊነት ነው። እንሰሶች እንኳን ራሳቸውን ከአውሪዎች የሚጠብቁት በዓይነት በዓይነታቸው ተሰባስበው፣ ልጆቻቸውን በመሃል አድርገው እየተከላከሉ ኅበዞቻቸው ከፊት በመጋፈጥ የመጣውን አውሬ በህብረት በማጥቃት ነው። ይህ የተፈጥሮ ጉዳይ እንጂ የንቃተ ኅሊና ጉዳይ አይደለም። አማራው በማናቸውም ሥፍራ በሚኖርበት አካባቢ በውጭ ሃገርም ጭምር በቅጡ ሊሰባሰብና ሊደራጅ ስለሚገባ ቀድሞ በተቋቋሙለት የሞረሸ ወገኔ፣ ቤተ አምሃራ ወይንም መአሕድ ውስጥ ተመዝግቦ ራሱንና ወገኖቹን ሊያድን ይገባል። የሚሰባሰበውና የሚደራጀው ራሱን ከጥቃት ለመጠበቅ እንጂ ሌሎችን ለማጥቃት አይደለም። የሜዳ አይሆች ለብቻቸው ተሰባስበው አንበሳን የሚያህል ጠንካራ አውሬ ይቋቋማሉ፣ ያባርሩታል። ጎሾች ተደራጅተው አንበሳን የሚያህል ጠንካራ አውሬ ያቆስሉታል፣ አንዳንድ ጊዜም ይገድሉታል። የዱር እንሰሳት ባይደራጁና በመልክ መልካቸው ባይሰባሰቡ ኖሮ አንበሳ፣ ነብርና ጅብ እየነጠሉ ይጨርሳቸው ነበር። የዱር እንሰሳት ዘራቸው ሳይጠፋ የቀረው ተሰባስበው ኅልውናቸውን ስለሚጠብቁ ነው። የሜዳ አይሆች ተሰባስበው ሊያጠቃቸው የመጣውን አውሬ ሲከላከሉ ድንገት ደንብራ አንዲት ቀጭኔ መሃከላቸው ብትገባ ምንም አይሏትም። እንደማታጠቃቸው የተፈጥሮ ንቃት (instinct) አላቸው። ነገር ግን አንድ ቀበሮ ማህከላቸው ሊገባ ቢሞክር መግቢያ ቀዳዳውን ይደፍኑበታል። እሱም አውሬ እንደሆነ ይገነዘባሉ። በጎች ግን የዋህ በመሆናቸው እማህላቸው የበግ ለምድ የለበሰ ተኩላ ዘው ሲል አያስተውሉም። በእርግጥ ይህ ምሳሌአዊ አነጋገር ነው። እየሱስ ክርስቶስ በክርስትያኖች መሃከል እነሱን የመሰለ አሳሳች የበግ ለምድ የለበሰ ተኩላ ሊገባ እንደሚችል በምሳሌ አስተምሯል። መደራጀት ችግሮችም አሉት። አንድን ድርጅት ኅልውናውን የሚያፈርሱት እነሱን መስለው የሚገቡ ሠርጎ ገቦች፣ ሠላዮችና የመረጃ ሥራ አዋቂዎች ናቸው።

**ሰላዮችን እንደምን መለየት ይቻላል?**

ከላይ በምሳሌ እንዳቀረብኩት በጎች እነሱን መስሎ ውስጣቸው ሠርጎ የገባውን ተኩላ ሊለዩት አይችሉም። ምክንያቱም እነሱን እንዲመስል አስቀድሞ የበግ ለምድ ለብሷልና ነው። ሰዎችም ሰላይንና ሠርጎ ገብን በቶሎ አያውቋቸውም። እነሱን

ስለሚመስል፣ ፍላጎታቸውን ስለሚጋራ ባህርያቸውን ስለሚያንጸባርቅ፣ የወለዱትን ስለሚስምላቸው፣ የሚወዱትን ስለሚያወራ፣ ኃይማኖታቸውን ስለሚቀበል፣ ወዘተ፣ ሠላይን መለየት እጅግ አዳጋች ነው። ወያኔ ታላላቆቹን ነገዶች አማራውንና ኦሮሞውን ከፋፍሎ ቀጥቅጦ እየገደለ የከርሰ ምድሩን ኃብት ሊዘርፍ የቻለው እነሱን የመሰለ ሰው ውስጣቸው አስርጎ ማስገባት በመቻሉ ነው። አማራው - የወያኔው "አማራ ተብዬው ክፍል - ኢህድን" የበላይ አመራር የሆኑትን በረከትን አዲሱን ወይም ደመቀን በቅጡ ያውቃቸዋልና የሚሉትን አይሰማቸውም። አማራውን የጎዱት እነበረከት፣ አዲሱና ደመቀ በጥቅም የገዟቸው፣ ሎሌ ያደረጓቸው ሰርጎ ገብ አማራ ካድሬዎች ናቸው። እነዚህ የከፋት ሎሌዎች አሁንም እንኳን በአማራው እምቢተኝነት ንቅናቄ ውስጥ ስለሚሳተፉ የትግሉን አውራ መሪዎች እየሰለሉ ስሞቻቸውን ለወያኔ ገዳዮች ያስተላልፋሉ። ወያኔም እነዚህን ጀግኖች እየነጠለ በመግደል የነጻነት ትግሉን ለማዳከም ይሞክራል። ደርግ (በሁሉም ኤርትራውያንና ትግራዋዮች ማለቱና ማጠቃለሉ ትክክል ባይሆንም እንኳን) ዙርያውን በሻዕቢያ ደጋፊ ኤርትራውያኖችና በወያኔ ደጋፊ ትግሬዎች የተከበበ፣ ራሱን አስቀድሞ ያጠፋ መንግሥት ነበር። ደርግ የተሸነፈው በውጊያ ሳይሆን የራሱን መረጃ በምስጢር መጠበቅ አለመቻሉና የጠላቱን የተዛባ መረጃ በትክክል አለመተርጎሙ ነበር። የደርግ ወታደራዊና ሲቪል ደህንነቶች ከሙያ አኳያ እታች ድረስ ወርደው መሠለሉን ስለሚንቁት፣ እነ ስብሃት በአንድ ኮሎኔል ቤት ዘበኛ ሆነው የደርግን እንቅስቃሴ በመቆጣጠር መረጃ ይጠልፉ ነበር። በሌላ በኩልም "ቆርቆሮ ያሌው"፣ "ልዋጭ ልዋጭ" "ዘንቢል ዘንቢል" እያሉ እበራፍ ድረስ እየመጡ እያንዳንዱን ሰው የሚሰልሉትን የወያኔና ሻዕቢያ ሰላዮችን ደርግ ፈጽሞ ሊውቃቸው አልቻለም፣ እንኳንስ ማወቅ ቀርቶ ይህ ድርጊት ይከናወናል ብሎ ደርግ ከቶውንም አልጠረጠረም ነበር።

ሰላዮችን መለየት እንዲህ በቀላሉ ቀላል አይደለም። ለምሳሌ በደርግ ጊዜ የሻዕቢያ ደጋፊን ኤርትራዊ መለየት ቀላል አልነበረም። ይህ ሰላይ ባለገንዘብ ከሆነ ለሚሰልለው ጎረቤቱ ስጦታ በማምጣት በደግ ሥራ ስም ራሱን ደብቆ አብሮ እየበላ እየጠጣ አበልጅ እስከመሆን ሊደርስ ይችላል። "የዋህ እንደ በግ" የሆነው ጎረቤቱ ይህን "የበግ ለምድ" ለብሶ የመጣውን ኤርትራዊ የሻዕቢያ ሰላይ እንደምን ማወቅ ይችላል? በእርግጥ ይህ ሰው ራሱን ሊጠብቅ የሚችለው ስጦታውን ባለመቀበል ወይንም ስጦታውን ተቀብሎም ቢሆን ልቡን፣ ቤቱን ገመናውን በመደበቅ፣ ነቃ ያለ ከሆነ ደግሞ በጸረ መረጃ ስልት የሰላዩን ተልዕኮ በማብከን ነበር። ዛሬም ቢሆን በርካታ የወያኔና ሻዕቢያ ደጋፊዎች በውጭ ሃገራት በሚገኙት ማህበራት ውስጥ አባላት ናቸው። መግባት የማይችሉት ደግሞ የማህበራት መሪዎችን ወይም የፖለቲካ ፓርቲ አባላትን ጓደኛ በማድረግ በስብሰባው ላይ ምን እንደተባለ፣ ምን እንደተወሰነ፣ ምን እንደታቀደ ወሬ መቃረም ብቻ ሳይሆን ማህበሩ ደካማ እንዲሆን ጓደኛ ተብዬውን የስህተት ትምህርት ካስጨበጡት በኋላ ንዝህላልና ግድየለሽ አድርገው ከፖለቲካና ማህበራዊ ተሳትፎ ራሱን እንዲያገል ይመክሩታል። ድራፍትና ውስኪ እያጠጡት ወይንም ክትፎ እያበሉት አልያም ሚስቱ የምትወደውን ቀሚስ ወይንም ሽቶ በስጦታ ስም እየሸለሙ ቤተኛ የሆኑ ሰላዮችን መጠራጠሩ "ለየዋሁና እምነት ለገዛው ኢትዮጵያዊ” ቀላል አይደለም። ወይ ነዶ! የዋሁ አማራ ብልጥ እንደ እባብ በሆኑት መሠሪዎች ተታልሎ ሚኒልክ ቤተመንግሥት ድረስ ሸኛቸው።

በውጭ ሃገራት የሚገኙ ሻዕቢያ አስቀድሞ በደጋፊዎቹ አማካኝነት የመሠረታቸው የጴንጤ ቤተክርስትያኖች በርካታ አማሮችን አዘናግተው፣ አፍዝዘው፣ ገዝግዘው ሲጋልቡባቸው ከመቆየታቸው በተጨማሪም ከነዚሁ ምስኪኖች በመባና እርዳታ ስም የሚሰበሰበው ከፍተኛ ገንዘብ በተወካዮቹ አማካኝነት ወደ ሻዕቢያ ካዝና ሲላክ ቆይቷል። በተለይ ተሰደው መልስ ያላገኙ ሰዎች ከጭንቀታቸው ለመገላገል በስደቱ ጉዳይ የብዙ ጊዜ ልምድ ያሏቸውን የሻዕቢያ ደጋፊ ኤርትራውያኖችን ከመጠጋት ውጭ ሌላ አማራጭ ስላልነበራቸው ኤርትራውያኑን ወዳቋቋሙት በእነሱ አባባል “የአማርኛ ተናጋሪዎች ቤተክርስትያን" ሄደው አባል ሆነዋል። እነዚሁ ምስኪን አማሮች መልስ ቢያገኙም እንኳን በውለታ ታስረው የብዙ ሻዕቢያ ደጋፊ ኤርትራውያኖች ተገዢ በመሆናቸው፣ መባዎቻቸውና ምፅዋቶቻቸው የሻብያን ካዝና እየሞላ ሳያውቁትየገንጣዮቹን መንገድ አደላድለዋል። መልስ አግኝተው፣ ሥራ ይዘው፣ ኋላም እዛው ቤተክርስትያን የተዳሩት የዋሆቹ ሻዕቢያ ሲጫወትባቸው የቆዩትን አማሮች ወያኔ በተራው ተረክቧቸዋል። በርካታ አማሮችበወያኔ ኤምባሲ ተላላኪዎች ተደናብረው ሲያበቁ ከወያኔ ላይ አንዲት ዛኒጋባ መቀለሻ ቦታ ተረክበው ለወያኔ ከፍተኛ የገቢ ምንጭ በመሆን እንደገና ለሌላ ጥፋት ተዳርገዋል። እነዚህ በዓመት ሁለቴ ወይም ሶስቴ በኢትዮጵያ አየር መንገድ እየተመላለሱ ዛኒጋባዎቻቸውን የሚቀልሱት የዋህ አማሮች ለወያኔ ጥይት መግዣ ገንዘብ አስተዋጾ በማድረግ በርካታ አማሮችን፣ ኦሮሞዎችን፣ ጋምቤላዎችን፣ ቤንሻንጉሎችን፣ ኮንሶዎችን በማስፈጀት ሳያውቁት ለትግራዩ ነጻ አውጭ ድርጅት የእጅ አዙር እርዳታ አድርገዋል። ኦሮሞዎች አስቀድመው የራሳቸውን ቤተክርስትያንና ማህበራት የመሰረቱት ትግላቸው በወያኔ እንዳይታነቅ ነው። በአራዶች አነጋገር ኦሮሞዎቹ ከአማራዎች ይልቅ “ነቄ” ነበሩ።

ባጠቃላይ በደርግ ጊዜ ከሱዳን፣ ኬንያ፣ ጅቡቲና ከሌሎች ሃገሮች ጭምር በሻዕቢያ "የስደትና ማሰደድ ክፍል" ድጋፍ ወደ አውሮፓ፣ አሜሪካ፣ አውስትራልያና አረብ ሃገሮች ተሸጋግረው ለራሱ ለሻዕቢያ የገንዘብ ምንጭ የሆኑትን እነዚህን ምስኪን አማሮች ኋላም ወያኔ ከሻዕቢያ ነጥቆ ቦታ እየሰጠና በኢንቨስትሜንት ስም እያሞኘ ወተታቸው የሚጋትባቸውን አማራዎችን በማንቃት ይልቁንም ሃገር ቤት ያለውን ወገናቸው አማራን ከእልቂት እንዲያድኑ ለማድረግ በአማራው ድርጅቶች ውስጥ እንዲሰባሰቡ መጎትጎቱና ማንቃቱ የግድ አስፈላጊ ነው። ሻዕቢያና ወያኔ እሳካሁን ድረስ ከላይ በጠቀስኳቸውና ወደፊት በሚገለጹ ስልቶች አማካኝነት አማራውን ተቀራምተውታል። የአማራው መደራጀት በርካታ የባከኑ ነገሮችን

አስተካክሎ እንደገና ለጠቀሜታ ያውለዋል። ሃገር ቤት ያለውን ምስኪን አማራ ከእልቂት ለማዳን ድርጅቱ የሚከፍተው የሬዲዮ ወይንም ቴሌቪዥን ጣብያ ውጭ በሚገኙ በርካታ አማሮች ሊታገዝ ይችላል። የአማራው ሬዲዮና ቴሌቪዥን ጣብያ በወልቃይት ሕዝብ ላይ ገና አስቀድሞ የጭካኔ ሥራ የሠሩትን የወያኔ ወንጀለኞችን መድረክ ይነፍጋቸዋል። የአማራው ሬዲዮና ቴሌቪዥን ጣብያ ለአማራው፣ ድምጹን ለተነፈገው አማራ፣ ድምጽ ይሆናል እንጂ የነፍሰ ገዳዮች መድረክ አይሆንም። ጣብያው አማሮችን ከደቡብና ምዕራብ ኢትዮጵያ ያፈናቀሉትን ጸረ አማሮች ለፍርድ እንዲቀርቡ ማስረጃ እንዲሰበሰብ የበኩሉን አስተዋጾ ያደርጋል። ጣብያው በቁሙ አንገቱን እንዲደፋና እንዲሸማቀቅ ለተደረገው፣ በሚያሳፍር ስድብና ማንቋሸሽ ኅልውናውን እንዲስት፣ በሃያ አምስቱ ዓመታት በግፍ እንዲፈጅ፣ በየጉድጓዱ በህይወቱ እያለ እንዲጣል፣ ይህ አልበቃ ብሎ በሠላም በተሰበበት ቦታ በአጋዚ አልሞ ተኳሾች እልቂት ለሚፈጸምበትና ዘሩ ለመከነበት የአማራው ነገድ ተቆርቋሪ፣ ታጋይና አታጋይ ይሆናል።

የአማራው ለብቻው መደራጀት ሰላዮችና ጸጉረ ልውጦች እንደቀድሞው ዘው እንዳይሉ ይገታል፣ ምርመራ ያደርጋል። ለምሳሌ እርሱ አማራ ሆኖ ሚስቱ የወያኔ ወይንም ሻዕቢያ ደጋፊ የሆነች ሰውን ወደ ድርጅቱ እንዳይገባ መከልከል ባይቻልም እንኳን የድርጅቱ የደህንነት ክፍል ክትትል ያደርጋል። አመኔታ ብቻውን ውድቀት ያስከትላል። በደርግ ዘመን አንድ ጄነራል፣ ከፍተኛ የጦር ኤታ ማዦር፣ ሚስታቸው የሻዕቢያ ደጋፊ እንደነበረች ይወራል። በሚስታቸው አማካኝነት ውጭ ሃገር ሕክምና ላይ እንዳሉ ከሻዕቢያ ጋር የተዋወቁት ጄኔራሉ ስህተታቸው ደርግን ብቻ ሳይሆን የቀድሞው ሠራዊት እንዲፈራርስ ትልቅ አስተዋጾ ሳያደርግ አልቀረም። ሻሸመኔ ተወልዶ ያደገው አማርኛና ኦሮምኛ አቀላጥፎ የሚናገረው ትግሬው ወርቅነህ ድንገት ተሰዶ አማራው ወይንም ኦሮሞው ድርጅት ውስጥ ቢገባ ምን ያህል ጥፋት ሊፈጽም እንደሚችል ማወቁ አዳጋች አይደለም። ስለሆነም ከነዚህ ዓይነቱ ተሞክሮ በመማር የአማራው ድርጅት ራሱን በመረጃ ሥራና መረጃ አሰባሰብ ሙያ ላይ አጎልብቶ እታች ድረስ ወርዶ እየተቆጣጠረ ዘወትር ራሱን ከጥፋት መጠበቅ ይኖርበታል። በተለይም በውጭ ሃገሮች መጠርያዎቻቸውን ሆነ ዘራቸውን ሳይቀር የቀያየሩ በርካታ "ወርቅነህ ገበየሆች" አሉና ማንንም አባል ከማድረግ በፊት ጥናት መውሰዱ ጠቀሜታ አለው። እንደ ጄኔራሉ ሚስትና ወርቅነህ ያሉ የሻዕቢያና ወያኔ ተልዕኮ አስፈጻሚዎች የሰላሳና ሃገር የማፍረስ ሥራቸው ተወርቶም ሆነ ተጽፎ አያልቅም። ጓደኛ፣ ቤተኛ፣ አበልጅና ረዳት በመሆን እያጃጃሉ ኢትዮጵያን አፍርሰዋል። ከዚህ በኋላ ግን ሞኝ መሆን አይገባም።

**የአማራው ለብቻው መደራጀት ኢትዮጵያዊነትን ያዳክማል?**

አንድ ወቅት ላይ አፍቃሪ ወያኔ የሆነው የኢትዮጵያ ፈርስት ድረገጽ አዘጋጅ ቤን የተባለው ጋዜጠኛ አቶ መለስንና አቶ ሽፈራው ሽጉጤን ቃለመጠይቅ አቅርቦላቸው ነበር። አቶ መለስን እንዲህ ሲል ጠየቃቸው።(ቃለ መጠይቁን ስለረሳሁት ሃሳቡን እንጂ ቃል በቃል ላስቀምጠው አልቻልም)። "እንደው ኦሮም ኦሮሞ ሲባል ይለጠጥና ኢትዮጵያዊነትን አያዳክምም?" እርሳቸው ሲመልሱም "አያዳክምም - ኦሮሞው በኦሮሞነቱ ማንነቱ ሲከበርለትና እውቅና ሲሰጠው እንደውም ኢትዮጵያዊነት ያጠናክራል" አሉ። በሌላ ጊዜ ደግሞ አቶ ሽፈራው ሽጉጤን ጠየቃቸው። "እንደው ይህ በዘር በዘሩ መደራጀት ኢትዮጵያዊነትን አያላላም፣ አያፈርስም?" እሳቸውም እንደ አለቃቸው ሲመልሱ "አያዳክምም - ለምሳሌ እኔ ሲዳማ ነኝ፣ ሲዳማነቴ ሲታወቅልኝና ማንነቴ ሲከበርልኝ ኢትዮጵያን እወዳታለሁ። ስለሆነም ኢትዮጵያዊነት ይጠናከራል"። ሁለቱም መልሳቸው ላይ ማንነት (identity) የምትለዋን ጽንሰ ሃሳብ አንስተዋል። ማንነታቸውን ያወላገደባቸው አማራ ነው ወይንም ሁሉንም ገዥዎች አማሮች ናቸው ለማለት ነው። ይህ የተሳሰተ ፍልስፍና፣ ወደ ስልጣን ላይ ለመውጣት የተፈበረከ፣ ይህ እኩይ ፍልስፍና ነው አማራውን ያስጠቃው። ወያኔና ሻዕቢያ የሁሉም ዘር ጠላት አማራ ነው ሲሉ ለልጆቻቸው እያስተማሩ በምስኪኑ አማራ ላይ የግፍ ጣታቸውን ቀሰሩበት። አማራው የተሳለቀበትና ማንም እየተነሳ የሚያንቋሽሸው በዚህ ፍልስፍና፣ እዛው ደደቢት ውስጥ በተቀመረው የተሳሳተ ርኩስ ንድፈሃሳብ ነው።

አማራው ለብቻው መደራጀቱ ኢትዮጵያዊነትን ሊይዳክም ይችላል ተብሎ ይፈራል። አንዳንዶች ደግሞ አማራው ትልቅ ነገድ በመሆኑ ራሱን ሲያገል በሌሎች ነገዶች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊከሰት ይችላል ይላሉ። አማራውና ኢትዮጵያዊነት ግን አይነጣጠሉም። ኢትዮጵያ እግዚአብሄር አምላካችን ቃል የገባላት ሃገር በመሆኗ አትፈርስም። ሻዕቢያና ወያኔ ያጣመሙትን ለማስተካለል አማራና ኦሮሞ በስልት ደረጃ በተናጠል እየታገሉ በተመሳሳይ ግብ ላይ ያነጣጥራሉ። ይህ ወቅቱና የትግሉ ባህርይ የፈጠረው ጉዳይ ነው። አማራና ኦሮሞው የጋራ ጠላታቸው የሆኑትን ሻዕቢያንና ወያኔን ለማዳከም አሁን የሚከተሉት የትግል ስልት አመርቂ ነው። ጎንደር ላይ ከፍ ብሎ የተነበበው "የኦሮሞው ወገኔ ደም የኔም ነው" የሚለው ናዝሬት ላይ "የአማራው ወገኔ ደም የኔም ነው" የሚል ታሪካዊ ምላሽ አገኘ። ይህ የደደቢቱን ፍልስፍና አፈር ድሜ ያስጋጠው መፈክር፣ ወያኔን ሲጋቶራው እንደተራገፈ ዱንያ ባዶ አድርጎታል። ባጠቃላይ ሌሎቹ ትናንሾቹ ብሄረሰቦች በወያኔና ሻዕቢያ እንዳይጨፈለቁ ዋነኛ አጋር ሊሆኑላቸው የሚችሉት አማራውና ኦሮሞው ናቸውና እውስጣቸው ያሉትን እንደነ ተሾመ ቶጋና ሽፈራው ሽጉጤ ያሉትን መሠሪዎች አንቅሮ በመትፋት መስመራቸውን ማስተካከል

ይገባቸዋል። ኢትዮጵያ ፌደራል መንግሥት የላትም። የዛሬይቱ ኢትዮጵያ በቀማኞችና ሙሰኞች የምትደዳደር ስትሆን እነዚህኑ ቀማኞች የሚጠብቅ ፌደራላዊ የገዳዮች ኃይል (ዓግአዚ) ነው ያለው። ለሕጻናት፣ ለሙሽሮች፣ ለቆነጃጅት፣ ለባልቴቶችና አዛውንት ለተማረ ወጣትና ጉብል የማይሳሱት እነዚህን ጨካኝ ኃይል ለመደምሰስ መፍትሄው ሕብረትና ትግል ብቻ ነው። ኮንሶው፣ ጋምቤላው ጉራጌውና ቤንሻንጉሉ የአማራውንና ኦሮሞውን ኢጋዥነት ይፈልጋሉ። አማራና ኦሮሞውም የነሱን ኢጋዥነት ይፈልጋሉ። የአርባ ዓመቱ የሻዕቢያና ወያኔ ርኩስ ርዕዮተ ዓለም ከተንኮታኮተ የአፍሪካ ቀንድ አህጉራት ኤርትራን ጨምሮ በሰላም ይኖራሉ።

የእሬቻ እለት እሁድ (2 oct 2016 ዓም) ወያኔ-አግዓዚ ቢሾፍቱ ላይ ከሶስት እስከ አምስት መቶ በሚደርሱ ሠላማዊ ሰዎች፣ ቆነጃጅት የኦሮሞ ልጃገረዶች፣ ወጣቶች ላይ እልቂት ያወጀው ከእብደትና ፍርሃት የተነሳ ነው። የቢሾፍቱው እልቂት 21 March 1960 በደቡብ አፍሪካ አፓርታይድ ፖሊሶች የተፈጸመው ከ 69 ሰዎች በላይ ከቀጠፈው የሻርፔቪል እልቂት (Sharpeville Massacre) እንዲሁም 4 June 1989 በቻይና ቲያናሜን አደባባይ (Tianamen Square Massacre) ከተፈጸመው ከ 500 – 2600 ሰዎች በላይ ነፍስ ካጠፋው እልቂት መሃል ይገኛል። የቢሾፍቱው እልቂት (Bishoftu Massacre) በአለም ላይ ከተፈጸሙት ዘግናኝ እልቂቶች መሃከል እንደ አንዱ ሆኖ በዊኪፔድያ ይመዘገባል።

የትግራይ ነጻ አውጭ ነን የሚሉት ኤርትራውያን፣ የአማራው የቅርብ ወገን የሆነውን የትግራይ ሕዝብ ተባባሪዎቻቸው አድርገው፣ በፌደራሉ የገዳዮች ድርጅት (ዓግአዚ) ከላይ የተጠቀሱትን ዓይነት ግፍና እልቂት እየፈጸሙ፣ ሕወሃቶች ይህ ዘግናኝ የበደል ፍጻሜ ታሪክ በአቶ ኃይለማርያም ትዕዛዝ ሰጪነት እንደተከናወነ ተደርጎ በዓለማቀፍ ደረጃ ሲመዘገብ ደንታም የላቸው። እነርሱ ከሂትለር ይልቅ ልዩ ልዩ የክፋት ስልቶችን የተላበሱ ቀማኞች፣ ዘራፊዎችና ሙሰኞች ናቸው። ተላላው ወንጀለኛ አቶ ኃይለማርያም አማራው እንዲገደል የሰጡት ትዕዛዝ (አዋጅ) እስካሁን ድረስ አልተነሳም።

አማራ ለዘላለም ይኑር፤ ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር

DOWN - DOWN - TPLF
DOWN - DOWN - Woyane